# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡፡
# Ethiopia: The Kingdom of God

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

---

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሓዱ አምላክ።**

**በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወመድኀኒትነ፡ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፡**
**እንተ ይእቲ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፡ በእንተ ኵሉ**
**ዓለም፣ ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥት፥ ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ።**

**በስመ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ዘቤዘወነ በመስቀሉ፥**
**ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ-ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፣**
**አንበሳ መዋኢ፥ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ሥርዉ ለዳዊት፣**
**ንጉሠ-ጽዮን፥ ወንጉሠ-ነገሥት፥ ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ።**

---

ይድረስ፡-

በደቡብ ጎንደር፣ በላይ ጋይንት አውራጃ፥ በነገላ ወረዳ፣ በታች ነገላ ንኡስ ወረዳ፣ በቀበሌ ፳፫ (ሃያ ሦስት) ውስጥ ከሚኖሩ፡ ከሰባቱ ሰበካ ጉባኤዎች ተመርጣችሁ፡ በእንደራሴነት ለምታገለግሉ፡ ለሰባቱ የምርፋቅ አባሎች፥

ደግሞም፡ የእኛ፡ ተወካዮች ኾናችሁ ለምታገለግሉት፡ ለቄስ ጌቴ አበባው እና ለአቶ ወንድሙ መለሰ፤

ዘካርያስ ከተማ (የሰኞ ገበያ)።

ኹላችሁንም በአንድነት፡ "እንደምን አላችሁ?" እያልን፡ የናፍቆትና የፍቅር ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን፤ አምላከ-ዘካርያስ ይክበር ይመስገን፡ እኛ፡ ደኅና ነን።

አዎን! እናንተም፥ እኛም፡ በያለንበት፡ ደኅና በመኾናችን፥ ይህንኑም ዜና፡ በየምክንያቱና በየአጋጣሚው፥ በየጊዜው ስለምንሰማ፡ ደስ እያለን፡ እናንተንም፥ እኛንም፡ በልዩ ቸርነታቸው፡ በያለንበት፡ በሕይወትና በጤንነት ለሚጠብቁን፡ ለፈጣሪያችን፡ ለልዑል እግዚአብሔርና ለቅድስት እናቱ፡ ለድንግል ማርያም፡ "የዘወትር ምስጋናችን፡ ያለማቋረጥ ይድረሳቸው!" እንላለን።



መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፣ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፣ ፳-00-፹፭፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekw@ethkogserv.org
**Website: www.ethkogserv.org**
**Facebook: ethiopiathekingdomofgod**

ከዚህ በማስከተል፡ በእኛ በኩል፡ ልንገልጥላችሁ የፈለግነውን፥ በእናንተም በኩል ልታውቁት የሚገባውን፡ አንድ ታላቅ ቍም-ነገርን እናቀርብላችኋለን። ይኸውም፡ እንዲህ፡ በሚል ቃል፡ በዝርዝር ሠፍሮ የሚነበበው ነውና፡ ልብ ብላችሁ ተመልከቱት፡-

፩ኛ. በንዋየ-ክርስቶስ አምላክ አሳሳቢነትና አነሣሽነት፡ ከጥቅምት ፫ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም ረገድ ያለውን፡ ኹለንተናዊ መልካም ሕይወታችሁን፡ ወደተሻለ የልማት ዕድገት ከፍ ለማድረግ በማሰብ፡ እኛም፡ ከእናንተ ጋር ተባብረንና ተጋግዘን፡ በምክርም ኾነ በተግባር፡ በተቻለን ዓቅም፡ አስተዋጽኦዋችንን እያበረከትን፡ ይኸው፡ እስካኹን ዐብረናችሁ እየሠራን እንደምንገኝ ታውቃላችሁ።

በአኹኑ ጊዜ፡ እየደረጀና እየተጠናከረ፥ እየተስፋፋም በመኼድ ላይ ያለው፡ ይኸው የኅብረት ልማት ሥራችሁ፡ የወደፊት ዕድገቱ፡ በበለጠ ቅልጥፍና እየሠመረና እየተቃና ሊቀጥል፥ ለከፍተኛ ፍሬያማነትም ሊበቃ ይችል ዘንድ፡ ቀድሞውኑ የተመሠረተበትን ኢትዮጵያዊ ባሕርዩን ሳይለቅ፡ ሕጋዊ ሥርዓትን ይዞና በዘመናዊ መልክ ተዋቅሮ እንዲቋቋም የማድረጉ ገጽታ፡ እጅግ አስፈላጊ ከኾነበት ደረጃ ላይ መድረሱ፡ እነሆ ይታያል።

ይህም፡ ገና ከበፊቱ፡ የተነሣንበትንና የተያያዝነውን፡ የዕውቀት፥ የአገልግሎትና የልማት አካኼዳችሁን፡ በተፋጠነ ይዘት ገፍተንበት፡ ከታለመለት ስኬታማ ግቡ እንድናደርሰው የሚያስችለንን፡ ቀጣዩን ተግባር እንድንፈጽም በመገደዳችን ተከሥቷል።

ልንፈጽመው የተገባን፡ ቀጣዩ ተግባርም፡ በኢትዮጵያዊው ወግ፡ በቃል ኪዳን ተመሥርቶና ተቋቁሞ፡ እስካኹን ሲሠራ የቆየው፡ ይኸው የኅብረት ሥራችሁ፡ አኹን፡ በሕጋዊ ጽሑፍና በድርጅታዊ መልክ ተዘጋጅቶ፡ ይህ እውነታ የተገለጸበትን <u>ማቋቋሚያ እና መመሪያ ሥርዓት፡</u> ለማቅረብ መቻላችን ነው። እንዲህ ኾኖ የተዘጋጀውንም፡ የድርጅቱን፡ ማቋቋሚያ እና መመሪያ ሥርዓት ጽሑፍ፡ ይኸው፡ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከንላችኋል።

ስለዚህ፡ ከኹሉ አስቀድሞ፡ እናንተ አኹን ያላችሁት፡ የሰባቱ ሰበካ ጉባኤዎች ተወካዮች የኾናችሁ፡ ሰባታችሁ አባሎች፥ እንደተለመደው፡ ቄስ ጌቴ አበባውና አቶ ወንድሙ መለሰ በተገኛችሁበት ተሰብስባችሁ፡ በመጀመሪያ፡ ከላይ፡ በ፩ኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰውን፡ ይህንኑ የድርጅታችሁን <u>የማቋቋሚያ እና የመመሪያ ሥርዓት ጽሑፍ፡ ከነዐባሪዎቹ፡</u> በማስተዋልና በጥንቃቄ ትመለከቱታላችሁ፤ ማለትም፡ ዐብራችሁ ኾናችሁ፡ በንባብ ትሰሙታላችሁ። ምናልባት፡ በውስጡ የሚስተካከል ነገር ካገኛችሁበት፡ ታስተካክሉታላችሁ፤ የምታስተካክሉት ነገር ከሌለ፥ ተስማምታችሁ የተቀበላችሁት ከኾነም፡ ይህንኑ ውሳኔያችሁን፡ በቃለ-ጉባኤ ትመዘግቡታላችሁ።

ከዚያ በኋላ፡ ይኸው ውሳኔያችሁ፡ በሰባቱም፡ የሰበካ ጉባኤዎቻችሁ ዘንድ፡ እንዲታወቅና እንዲጸድቅ አድርጋችሁ፡ በዚህ፡ በጸደቀው ሥርዓት መሠረት፡ ይህን የጀመራችሁትን ኅብረታዊ የልማት ሥራ፡ ከፈጣሪያችሁ፡ ከልዑል እግዚአብሔርና ከቅድስት እናቱ፡ ከድንግል ማርያም በስተቀር፡ የማንም ፍጡር፡ የበላይ አዛዥነትና አጋዥነት ሳያስፈልጋችሁ፡ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ ራሳችሁን ችላችሁ፥ በራሳችሁ ሥልጣን የምታካኺዱት ይኾናል።

፪ኛ. በዚህ መልክና ይዘት ተመሥርቶና ተቋቁሞ ሲሠራ የቆየው፡ ይኸው ድርጅታችሁ፡ ከመጀመሪያው የወጠነውንና እያካኼደ ያለውን፡ ጊዜያዊዉንና ሥጋዊዉን፥ ምድራዊዉንና ተፈጥሮአዊዉን ብቻ ሳይኾን፥ ዘለዓለማዊዉንና መንፈሳዊዉን፥ ሰማያዊዉንና ኪዳናዊዉን፥ በአጠቃላይም፡ ሰብአዊዉንና ኹለንተናዊዉን፥ በይበልጥ ግን፡ ኢትዮጵያዊዉንና እግዚአብሔራዊዉን፡ የተቀደሰ ዓላማውንና ተግባሩን ጭምር፡ ከግብ ለማድረስ፥ ይህም ማለት፡ ፍጹም ፍሬያማ የኾነ፡ የኑሮ ልማትንና የሕይወት ዕድገትን፡ በፍጹም እርግጠኛነትና በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያስገኝላችሁ፡ በእውነት ከፈለጋችሁ፡ በቅድሚያ ልትፈጽሙት የሚገባችሁ፡ ኢትዮጵያዊ ውዴታ አለ፤ ይህም፡-

ሀ. እያንዳንዳችሁ የድርጅቱ አባሎች የኾናችሁት ወንዶችና ሴቶች፡ የድርጅታችሁ፡ **የማቋቋሚያው እና የመመሪያው ሥርዓት** አካላት ኾነው፡ ከእርሱ ጋር ተያይዘው የሚገኙትን፡ **"የቅዱሱ ኪዳን፡ የዘወትርና የመግቢያ ሙሉ ጸሎት"**፤ ደግሞም፡ **"የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት: የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ኢትዮጵያዊነት መገለጫ ክታቦች፤ ከእምነት ታማኝነት ማረጋገጫቸው ጋር።"** በሚል አርእስት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በግእዝና በኢትዮጵያኛ፥ በእንግሊዝኛም፡ የተዘጋጀውን መዝገበ ሃይማኖት፡ በነፍስ ወከፍ፡ ዐውቃችሁት፡ የምትሰጡት የምስክርነት ቃላችሁ ነው፤

በ. ከዚያ ቀጥሎ፡ የኢትዮጵያዊነት እና የኢትዮጵያዊትነት መታወቂያችሁ የኾነውን፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከፈጣሪያችሁ ያገኛችሁትን፡ የአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ቀለማት ቀስተ-ደመናና ሰንደቅ-ዓላማ ምልክታችሁ የኾነውን፥ ዓይነቱንም፡ ከዚህ ጋር አያይዘን የላክንላችሁን ማተብ፡ በየአንገታቸው ላይ በማሠር የምትፈጽሙት ሃይማኖታዊ ሥርዓታችሁ ነው።

፫ኛ. ከዚህ ሌላ፡ በተጨማሪ፡ የምታደርጉት ገንቢ ተግባር ቢኖር፡ ይኸው ድርጅታችሁ፡ በሰዎች ዘንድ ታውቆና ተቀባይነትን አግኝቶ፡ እንዲሠምርላችሁ ከፈለጋችሁ ደግሞ፡ ይኸው፡ **የድርጅቱ፡ ማቋቋሚያ እና መመሪያ ሥርዓት** ጽሑፍ፡ በቀበሌያችሁ አስተዳደር ዘንድ ቢመዘገብ ስለሚጠቅማችሁ፡ በቅድሚያ፡ የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪ፡ አቶ ዘውዱ ተፈራን ታማክራላችሁ።

እርሳቸው፡ በዚሁ አሳብ የሚስማሙበት ሲኾን፡ ይህንኑ፡ **የድርጅቱን፡ ማቋቋሚያ እና መመሪያ ሥርዓት ጽሑፍ፡** ዋናውን፡ ለእናንተ እና በመዝገብ ቤታችሁ ተቀማጭ እንዲኾን አስቀርታችሁ፡ ግልባጩን፡ በብርሃናዊ ቅጂ አስነሥታችሁ፡ ከእርሱ ጋር በተላከላችሁ መሸኛ ደብዳቤ አማካይነት፡ **ታኅሣሥ ፲፰ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. የተጻፈውን ደብዳቤ** ጭምር፡ በዐባሪነት አያይዛችሁ፡ ለቀበሌው አስተዳዳር ጽሕፈት ቤት ገቢ ታደርጉታላችሁ።

፬ኛ. ከዚያ አከታትላችሁ፡ በተስማማችሁበት፡ በዚሁ፡ **በድርጅቱ የማቋቋሚያ እና መመሪያ ሥርዓት መሠረት፡** ከዚህ የሚከተሉትን ተልእኮዎች ትፈጽማላችሁ፡-

ሀ. ከሰባቱም የሰበካ ጉባኤዎች፡ ከእያንዳንዳቸው ተመርጠው የሚላኩትን፡ አምስት አምስት የምርፋቁን አባሎች ምርጫ እንዲካኼድ አድርጋችሁ፡ የተመረጡት አባሎች፡ በአካል እንዲሰበሰቡ በማድረግ፡ የድርጅቱን ምርፋቅ መቋቋም፡ በይፋ ታበሥራላችሁ፤ ታሳውቃላችሁ፤ ታረጋግጣላችሁ።

በዚህ በተቋቋመው ምርፋቅ ውስጥ፡ ቄስ ጌቴ አበባው እና አቶ ወንድሙ መለሰ፡ እንደማንኛችሁም ኹሉ፡ በቀበሌ ነዋሪነታችሁና በሰበካ ጉባኤ አባልነታችሁ፡ በምርፋቁ ውስጥ፡ በቅዱሳን ሐዋርያት አቦ ቤተ-ክርስቲያን፥ ወይም፡ በሌሎቹ፡ በአንዳቸው ሰበካ ጉባኤዎች በኩል ተመርጣችሁ፡ የምርፋቁ፡ ሙሉ አባሎች ልትኾኑ የምትችሉበት መብታችሁና ሥልጣናችሁ፡ የተጠበቀ መኾኑ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል።

ለ. በዚህ መልክ የተሠየመው ምርፋቅ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰብስቦ፡ በማቋቋሚያው እና በመመሪያ ሥርዓቱ ውስጥ የተጠቀሱትን፡ የድርጅቱን ሹማምንትና ተጠሪዎች፥ የአገልግሎት ባልደረቦችንም፡ ከመካከሉ መርጦ፡ በየሥራው የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ይመድባል።

ገ. የተመረጠው የሚመለከተው ኃላፊ፡ በድርጅቱ ስም የሚቀረፀውን ማኅተም፥ የሚታተሙትንም፡ የጽሕፈትና የሒሳብ ሰነዶችንና መዛግብትን አሳትሞ፣ መሣሪያዎችንም ገዝቶ ለአገልግሎት ያቀርባል።

ደ. ሌላው፡ የተመረጠው የሚመለከተው ኃላፊ፡ በአቅራቢያ በሚገኝ፡ በታወቀ ሕጋዊ ቤተ ንዋይ (Bank) ውስጥ፡ በድርጅቱ ስም፡ አስፈላጊ የኾኑ፡ የአደራ እና/ወይም፡ የወለድ ሒሳቦችን ይከፍታል። ምናልባት፡ ሕጋዊ ፈቃድ ባለመገኘቱ፡ በዚህ መልክ፡ ሒሳቦቹን መክፈት ባይቻል እንኳ፡ በድርጅቱ ሙሴ፥ በዋናው ጸሓፊና በዋናው ግምጃ ቤት፡ በሦስቱ ሹማምንት ስሞች፡ የቤተ-ንዋዩን ሒሳቦች መክፈት፥ ገቢና ወጪዎቹንም፡ በእነዚሁ፡ በሦስቱ ሹማምንት ጽሑፍ-ኪዳኖች (Firmas) ማንቀሳቀስ ይቻላል።

ሀ. በተከፈቱት ሒሳቦችም ውስጥ፡ ግምጃ ቤቱ፡ በእጁ ያለውን ጥሬ ገንዘብ ያስቀምጣል።

ወ. ምርፋቁ፡ የገንዘብ ዓቅሙ በፈቀደለት መጠን፡ አስፈላጊ የኾኑ የአገልግሎት ሥራዎችን እየከፈተና እያቋቋመ፡ ግዳጁን ያካኺዳል።

ዘ. አኹን፡ በቤተ ንዋይ ውስጥ ገቢ ከተደረገው ተቀማጭ ገንዘብ ላይ፡ በምርፋቁ እየተፈቀደ በሚደረገው ወጪ፡ እስካኹን የተጀመሩት፡ አንዳንድ የልማት ሥራዎች (ለምሳሌ፡ የከተማውን የኹለገብ አዳራሽ እና የዘካርያስን ትምህርት ቤት) ቢኖሩ፡ የእነርሱ ኺደቶች እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

፭ኛ. ከላይ በ፬ኛው ተራ ቍጥር የተዘረዘሩትን ተግባሮች፡ እውን ለማድረግ ያግዛችሁ ዘንድ፡ በእኛ በኩል፡ ዓቅማችን የፈቀደውን፡ የ፲፭ሺ (ዐሥራ አምስት ሺህ) ብር የአስተዋጽኦ በረከታችንን፡ በዚህ ደብዳቤያችን አማካይነት ልከንላችኋልና፡ ይኸው ተቀበሉን!

፮ኛ. የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማሳደሻ ድርሻውን፡ እስካኹን ሳያገኝ ለቆየው፡ <u>ለአቃሲኒ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ</u> የሚበረከት፡ ፲ሺ (ዐሥር ሺህ) ብር፡ ከዚሁ፡ ከ፲፭ሺው ብር ጋር፡ ዐብሮ ልከናልና፡ ይህንኑ አስተዋጽኦዋችንን፡ ለሌሎቹ እንደተደረገው ኹሉ፡ ቄስ ጌቴ አበባውና አቶ ወንድሙ መለሰ፡ ለዚሁ ሰበካ ጉባኤ፡ በደረሰኝ እንድታስረክቡልን ይኹን!

፯ኛ. እያካኺዳችሁ ያላችሁት፡ የልማት ኅብረታችሁ፡ አኹን በቀረበው፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ ተደራጅቶና ታውቆ እንዲቀጥል ማድረጉ፥ ማለትም፡ ይህ ድርጅታችሁ፡ በዚህ ኹኔታ ተሻሽሎና ተዋቅሮ እንዲሠራ መደረጉ፡ በእጅጉ የሚጠቅምበት ምክንያት አለ፤ ይኸውም፡-

አ. ከነገላ ውጪ፡ በኢትዮጵያም ኾነ፥ በባዕዳን አህጉርና በባሕር ማዶ የሚኖሩት፡ ያገሩ ተወላጆች የኾኑ፡ ወንዶችና ሴቶች፥ ወይም፡ ሌሎች በጎ አድራጊዎች፡ የአስተዋጽኦ በረከታቸውን፡ በገንዘብ ኾነ በቍሳቍስ፥ ወይም፡ በንብረት፡ ካሉበት ቦታ ኾነው፥ ወይም እየራሳቸው መጥተው፡ በቀጥታ፡ ወደድርጅቱ ቤተ-ንዋይ ሒሳባችሁ፡ ገቢ ሊያደርጉላችሁ፥ ወይም፡ በመልእክተኛ እንዲልኩላችሁ የሚያስችል፡ ቀናና ቀልጣፋ ዘዴ በመኾኑ ነው።

በ. የዚህ ድርጅት በዚህ፡ ሕጋዊ መልክና ይዘት እንዲዋቀር የመደረጉ እውነታ፡ በአገር ውስጥና በዓለም-ዐቀፉ የውጭ መገናኛ ብዙኃን አማካይነት፡ በበለጠ እንዲታወቅ ስለሚያስችል፡ የአስተዋጽኦ በረከቱን ፍሰትና መጠን፡ እጅግ ከፍ ሊያደርገው እንደሚቻል ስለታመነበት ጭምር ነው።

እንግዴህ፡ የስመ-ጥሩው ኢትዮጵያዊ ገድለኛ ሓዋርያ፡ የአለቃ ዘካርያስ፥ ወስመ-ጥምቀቱ ንዋየ-ክርስቶስ፡ ታማኞች ተከታዮች መኾናችሁ የሚገለጸው፥ ይልቁንም፡ የሰማዩ አባታችሁ፡ የቅዱስ እግዚአብሔር እና የእናት አገራችሁ፡ የቅድስት ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ እውነተኞች ልጆች መኾናችሁ የሚረጋገጠው፡ በነፍሳችሁና በሥጋችሁ፥ በመንፈሳችሁም፡ የማን ወገን መኾናችሁን፡ ለይተው የሚያሳውቁትን፡ እነዚህን፡ ከዚህ በላይ የሠፈሩትን፡ ሃይማኖታውያት ምግባራት፡ ፈጽማችሁ ስትገኙ ብቻ ነውና፡ ለምድራዊው መልካም ኑሮአችሁ እና ለዘለዓለማዊው የትንሣኤ ሕይወታችሁ ስትሉ፡ አኹን በምታደርጉት፡ በዚህ ትክክለኛ ምርጫችሁና ውሳኔያችሁ፡ የየግልና የጋራ ማንነታችሁን፡ በእየራሳችሁና ለእየራሳችሁ አስመስክሩ!

አምላከ ንዋየ ክርስቶስ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ረድኤትና በረከት፡ ለሰባቱ የአለቃ ዘካርያስ የነገላ ሰበካዎች፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንግሥት፡ የታሰበውንና የተወጠነውን፡ ይህን፡ የዕውቀት፥ የአገልግሎትና የልማት ዕቅድ፡ እስከዚህ የዕድገት ደረጃ ለማድረስ እንዳስቻለ ኹሉ፡ አኹንና ወደፊትም፡ በዚህ፡ በተዘጋጀው የተሻሻለ ድርጅታዊ መልክና ይዘት ቀጥሎ፡ ለመጨረሻው መልካም ፍሬ እንደሚያበቃው፡ በመለኮታዊ ፈቃዱ እንተማመናለን!

ጥቅምት ፰ ቀን፥ ፳፻፫ ዓ. ም.

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስም፡-

---

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ

ግልባጭ፡- ለደብረ ብርሃናት ቅዱሳን ሓዋርያት (አቦ) ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለጋርጥብና መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለአውችንድባ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለጩጫ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለሳዕም ቍስቋም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለጉድባ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለአቃሲጊ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ዘካርያስ ከተማ (ሰኞ ገበያ)፤ ታች ነገላ።